# አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**ANDINET NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (ANAASO)**

1334 9th Street, NW. Suite # 1 Washington DC. 20001.

Tel: (202) 462 0556 Fax: (202) 462 0557 Email: info@andinetusa.org


## ከአንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር የተሰጠ አስቸኳይ መግለጫ

### *የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ ለሚያቀርበው የትብብር ጥሪ ምላሽ መስጫው አሁን ነው!*

ጁላይ 21 2012

የአንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች አመራር ባደረገው ልዩ እና አስቸኳይ ስብሰባ በሃገራችን ኢትዮጵያ ያንዣበበውን ፈርጀ ብዙ አደጋዎች ተገንዝቦ፤ የመፍትሄ መንገዶችን በስፋት መርምሯል።

አምባገነኑ ህወሃት መራሽ የኢሃዴግ መንግስት በቆራጡ የዲሞክራሲ ታጋይ በአቶ አንዱአለም አራጌ ላይ የበየነውን የእድሜ ልክ እስራትና በእውቁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋም ሆነ በተቀሩት የዴሞክራሲ ሰላማዊ ታጋዮች ላይ ያስተላለፍውን የእረጅም አመታት የእስር ፓለቲካ ውሳኔ እጅጉን አምርረን እንቃወማለን። የሚይዘው የሚጨብጠው የጠፋው አምባገነኑ አገዛዝ በክርስቲያኑም ሆነ በእስላሙ ሃይማኖቶች ጣልቃ እየገባ የሚፈጥራቸው ቀውሶች ሃገራችንን ከማትወጣበት አዘቅት ውስጥ እየከተታት ስለሆነ ባስቸኳይ መቆም አለበት። እየተንገዳገደ ላለው አገዛዝ ተጨማሪ የጥፋት እድልም ሆነ ጊዜ መስጠት አይገባም። የዚህ ስርአት ቁንጮ የሆኑት የአምባገነኑ የአቶ መለስ ዜናዊ ክፉኛ የጤና መታወክን ተከትሎ በሃገርም ውስጥ ሆነ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ስለመጻኢ የሃገራችን እጣፈንታ እጅግ አሳሳቢ መሆን እየተወያየ ያለው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በአምባገነን አገዛዝ እድል ስለሌለው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የለውጥ ጥማት እውን ሳይሆን አያሌ እድሎች አምልጠዋል። ይህ አሳዛኝ ታሪክ ግን አሁን መቀየር አለበት። ለዚህም ዋናው ዋስትና ሕዝባችን እራሱን በፍጥነት አደራጅቶ ዘለቄታዊነት ያለው ዴሞክራሲያዊ የብልጽግና ስርአት መመስረት ሲችል ብቻ ነው።

**በመሆኑም አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር የሚከተሉትን ወቅታዊ ውሳኔዎች አሳልፏል፦**

1)በውጭው አለም ሆነው በሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲመሰረት ከሚታገሉ የፓለቲካ ድጋፍ ማህበራት/ቡድኖች/እንቅስቃሴዎች፤ የሲቪክ ድርጅቶች፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፤ የሃይማኖት ተቋማት እና ለሃገራችን ጉዳይ ከሚደክሙ ታዋቂ ግለሰቦች ጋር ተባብሮ መስራት ከምንጊዜውም በላይ ያለንበት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ስለሚጠይቅ ሙሉ ፈቃደኝነታችንንና ዝግጁነታችንን እንገልጻለን።

2)በተመሳሳይ መልኩ ሃገር ቤት የሚገኙት ተቃዋሚ ድርጅቶች ይዋል ይድር ሳይሉ በአስቸኳይ የመቀራረብና አብሮ በጋራ የመስራት ውል አስረው ለህዝባችን የአንድነት ጥሪ አፋጣኝ መልስ እንዲሰጡ አጠንክረን እያሳሰብን፤ ለዚህ አወንታም ሁለንተናዊ ድጋፋችን በተጠናከረ መልኩ እንደሚቀጥል እናረጋግጣለን።

3)በውስጥም ሆነ በውጭ ያለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለሃገራችን ህልውናና ለህዝባችን ነጻነት ሲል የትብብር ጥረቶቹ እውን እንዲሆኑ መላ ትብብር ያደርግ ዘንድ ወገናዊ አደራ እናስተላልፋለን። የለውጥ ጊዜው አሁን ነው በጋራ ተግተን እንስራ!